# እስክንድር ነጋና አንዷለም አራጌን ጨምሮ ጥቂት የሕሊና እስረኞች ከ እስር ቤት ወጡ

February 14, 2018



አንዱአለም አራጌ

ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን እና አንዷለም አራጌን ጨምሮ ጥቂት የሕሊና እስረኞች ዛሬ ከ እስር ቤት ተለቀቁ:: አሁንም በርካታ እስረኞች በግፍ እስር በተለያዩ እስር ቤቶች እየማቀቁ ይገኛሉ::

በዛሬው ዕለት ከ እስር ከተለቀቁት መካከል የህዝበ መስሊሙን ዉክልና በመቀበል ለዓመታት በእስር ቤት ሰሰቃዩ የነበሩት ጀግና የህዝብ ወኪሎች ኡስታዝ አህመዲን ጀበል፣ኡስታዝ አህመድ ሙስጠፋ፣ኡስታዝ መሐመድ አባተ ኻሊድ ኢብራሂም የሚገኙበት ሲሆን ከጋምቤላ ክልል መጥተው የታሰሩት የአኝዋክ ተወላጆቹ
ኦኬሎ አኳይ
ጋሌ ደንግ
ኦጂር ኦተው
ኦጁሉ ዌሎ
ኦዊር ኦጁሉ
ማንጋንፓት ኦብዎዶ
ኦሞቶ ኦዊል
ኦዳዩ ኦኬሎ
ኦጁሉ ኛው ከ እስር ቤት ወጥተዋል::




በዛሬው እለት ከተለቀቁት መካከል በነጀነራል ተፈራ ማሞ መዝገብ ተከሳ ለረዥም ጊዜ በ እስር ቤት ስትማቅቅ የነበረችው ወ/ሮ እማዋይሽ; ለረዥም ጊዜ የታሰሩት የኦሮሞ ፖለቲከኛ ኦልባና ሌሊሳ; በአርበኞች ግንቦት 7 ስም የታሰረው ብርሃኑ ተክለያሬድ; በነአንዷለም አያሌው የክስ መዝገብ የተከሰሱት እስክንድር ነጋና አበበ ቀስቶ ይገኙበታል::

በሌላ በኩልም ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬም ተለቋል:::

ዛሬ ከተፈቱት መካከል ጫልቱ ታከለ ትባላለች። ከኦነግ ጋር ግንኙነት አላችሁ ተብለው በ2000ዓም ከታሰሩ በርካታ ኦሮሞዎች መሃከል አንዷ ናት። የተፈረደባት 12ዓመት ሲሆን፤ ከ8 ዓመት በላይ በእስር አሳልፋለች። ጫልቱ በ እስር ቤት ከፍተኛ ግፍ ከሚፈጸምባቸው እስረኞች መካከል አንዷ እንደነበረች አብረዋት ታስረው የነበሩ ይመሰክራሉ::

ዛሬ የተፈቱት እስረኞች ቁጥር ወደ 700 የሚጠጋ ሲሆን አሁንም በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የሕሊና እስረኞች በግፍ እስር ላይ ይገኛሉ::

ትናንት ከ እስር የተለቀቁትና ዛሬ በአዳማ ከፍተኛ አቀባባል የተደረገላቸው አቶ በቀለ ገርባ ከ እስር ከወጡ በኋላ ለአሜሪካ ድምጽ በሰጡት ቃለምልልስ አካላቸው ጭምር በድብደባ የተጎዳ በርካታ እስረኞች መኖራቸውንና ይህም እንደሚያሳስባቸው ገልጸው መንግስት ሁሉንም እንዲፈታ መጠየቃቸው አይዘነጋም::